# Learning by Ear 2013

መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ -ከባድ አማራጮችን መጋፈጥ

EPISODE FIFTEEN: ምን ባደርግ ይሻላል?

**AUTHOR: Chrispin Mwakideu**

**EDITOR: Madelaine Meier, Ludger Schadomsky**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**SCENE 1: አቶ ካሳሁን AND አልማዝ MEET AT አቶ ካሳሁን'S HOUSE IN THE AFTERNOON**

- **አቶ ካሳሁን (M, 50)**
- **አልማዝ (F, 16)**
- **ወ/ሮ ለምለም (F, 40)**

**SCENE 2: በለጠ WITH THE SECURITY GUARD AT THE SCHOOL GATE**

- **በለጠ (M, 16)**
- **SECURITY GUARD (M, 60)**

**SCENE 3: ምህረት TALKS TO ትዕግስት IN THE SCHOOL LIBRARY ABOUT ዳንኤል 'S INVITATION**

- **ምህረት (F, 15)**
- **ትዕግስት (F, 15)**
- **LIBRARIAN (F, 50 )**

## SCENE 4: THE GUARD SNEAKS ምህረት INTO ዳንኤል ’S ROOM

- **SECURITY GUARD (M, 60)**
- **ምህረት (F, 15 )**

## 1. INTRO - NARRATOR:

ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ተከታታዮች። ይህ አፍሪቃ የሚገኙ ወጣቶችን ህይወት የሚያስቃኘውና "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" የተሰኘው ድራማ ነዉ። ወደ ዛሬው « ምን ባደርግ ይሻላል?» ወደሚለው 15ኛ ክፍል ከማለፋችን በፊት እስቲ ባለፈው የሆነውን መለስ ብለን እንቃኝ።

ቀደም ሲል ምህረት ለዳንኤል ስሜት እንዳላት ገልፃለታለች። ያ ግን ለሱ በቂ አልነበረም።

2. ዳንኤል (EP 13, 74): እንግዳውስ አሳይኝ። እንደምትይው እውነትሽን ከሆነ አረጋግጪልኝ።

3. ምህረት: " እንዴት አድርጌ ነው የማረጋግጥልህ?

4. ዳንኤል (78): በዚህ በሳምንቱ መጨረሻ ክፍሌ እንድትመጪ ጋብዤሻለሁ። ታድያ ብቻሽን እንደምትመጪ እርግጠኛ ሁኚ።

ምህረት ምን ማድረግ እንዳለባት አልወሰነችም። ዳንኤል በበኩሉ ተባባሪ አግኝተል። ጓደኛው በለጠ ሊረዳው ነገሮችን አመቻችቷል።

5. ዳንኤል (EP 14, 108): ስማ! እሺ! የተወሰነ ገንዘብ እና ሲጋራ ጀባ እልሃለሁ።." (…)

6. በለጠ: " እንደማላጨስ ታውቅ የለ… …"

7. ዳንኤል : "ባክህ ላንተ አይደለም። በሩ ላይ ላለው ጠባቂ ነው። ያንን ትሸጉጥለት እና ቅዳሜ ምሽት እንግዳ እንዳለህ እና እንድትገባ እንዲፈቅድላት ትነግረዋለህ። ያንተ ድርሻ ይህ ብቻ ነው። አለቀ!

እንግዲህ ነገሮች በእዚህ መልክ ተመቻችተዋል። ቆይ ግን ለመሆኑ ዳንኤል የሸሸገው ሚስጥር ነበር እንዴ? እስቲ ወደ ትውልድ ሀገሩ ላቦሪያ ወደ አባቱ አቶ ካሳሁን ቤት እናምራ። የዳንኤል የቀድሞ ፍቅረኛ አልማዝ እቤታቸው መጥታለች።

**SCENE 1: አቶ ካሳሁን AND አልማዝ MEET AT አቶ ካሳሁን'S HOUSE IN THE AFTERNOON**

8. **INTERIOR ATMO. LIVING ROOM WALL CLOCK TICKING**

9. **SFX: PEOPLE DRINKING TEA – CUPS ON SAUCERS ETC.**

10. **አቶ ካሳሁን:** **(orders)** ሰራተኛዋ የታለች? **(claps hands)** እነዚህን ስኒዎች አንሺ ባክሽ።

11. **SFX: HURRIED FOOTSTEPS APPROACHING**

12. **SFX: MAID TAKE CUPS AWAY AND LEAVES**

13. **አቶ ካሳሁን:** **(politely)** እሺ አልማዝ የኔ ልጅ፤ ምን ይምጣልሽ? እዚህ ቤት ምንጊዜም ብትመጪ በደስታ እንደምንቀበልሽ ታውቂያለሽ አይደል?! አባትሽ እና እኔ ከድሮ ጀምረን ብዙ አሳልፈናል። የወደፊቷ የልጄ ባለቤት ከመሆን ባለፈ ነው የማይሽ።

14. **አልማዝ:** አመሰግናለሁ አቶ ካሳሁን። ምንም አያስፈልግ።

15. **አቶ ካሳሁን:** ጥሩ፤ እሺ እንዴት ነው? አንቺ እና ዳንኤልስ እንዴት ናችሁ?

16. **አልማዝ:** **(clears throat)** ደህና ነን… ም… ምንም አንል።

17. **አቶ ካሳሁን:** ምንም አንል? ምን ማለትሽ ነው? በሁለታችሁ መካከል ችግር አለ እንዴ?

**18.** አልማዝ: እንደው እርስዎ ቢነግሩኝ አይመረጥም ብለው ነው? ስለ ዳንኤል ከሰማሁ ሶስት ሳምንት ሊሞላኝ ነው። ለመጨረሻ ያገኘሁት ጊዜ ባለፈው ስናወራ እንደ ሩቅ ሰው… እንጂ … ቀረቤታ እንደነበረን ሆኖ አላገኘሁትም።

**19.** አቶ ካሳሁን: እውነትሽን ነው? እንዴት እንዲህ ልትይ ቻልሽ? የነገረሽ ነገር አለ?

**20.** አልማዝ: አይ! ማለቴ በጣም አዝናለሁ አቶ ካሳሁን **(insecure)** ስለእዚህ ጉዳይ ከእርሶ ጋ ማውራቱ ጥሩ አይመስለኝም።

**21.** አቶ ካሳሁን: **(concerned)** አልማዝ፣ ከቻልኩ ልረዳሽ ብዬ እኮነው። እንግዲህ ልትነግሪኝ ፍቃደኛ ካልሆሽ ለማን ልትነግሪ ነው? ለእናቱ?

**22.** አልማዝ: ምናልባት… ከእሳቸው ጋ ባወራ ሳይሻል አይቀርም።

**23.** አቶ ካሳሁን: ባለቤቴን ታውቂያታለሽ። ግፋ ቢል ስለዚህ ጉዳይ ብትፀልይ ይሻላል ነው የምትልሽ። በቃ ይኼው ነው። ግን ስሚኝ ልጄ እኔ ላደርግላችሁ የምችለው ካለ --

**24.** አልማዝ: አቶ ካሳሁን እርስዎ ብዙ ነገር እስካሁን አድርገውልኝል። ይህ የዳንኤል እና የኔ ጉዳይ ነው። ለሻይ ግብዣዎ አመሰግናለሁ። በሉ አሁን ብሄድ ይሻላል።

**25.** አቶ ካሳሁን: መልካም። ለወላጆችሽ ሰላምታ አቅርቢልኝ። አባትሽን ደግሞ አመሻሹ ላይ ጎልፍ ክለብ ላግኝህ በይልኝ።

**26.** አልማዝ: እሺ አመሰግናለሁ። ደህና ይሁኑ።

**27. SFX: CHAIR BEING PULLED OUT**

**28.** አቶ ካሳሁን: ደህና ሁኚ ልጄ።

**29. SFX: FOOTSTEPS. አልማዝ LEAVES**

**30. SFX: MOBILE PHONE RINGS**

**31.** አቶ ካሳሁን: ሄሎ?

**32.** ወ/ሮ ለምለም: **(on the phone)** ሄሎ የኔ ውድ

**33.** አቶ ካሳሁን: ለምለም እንደዚህ አቆላምጠሽ መጥራቱን ብትተይውስ? ስለሁለታችን ማንም ሰው እንዲያውቅ አልፈልግም። በተለይ ደግሞ ባለቤቴ!

**34.** ወ/ሮ ለምለም: ምንም የሚያሰጋ ነገር የለም። ሚስጢር መደበቅ እችላለሁ። ስማ እስካሁን የወንድሜን ሁለት ወንድ ልጆች አላገኘኋቸውም። ምናልባት ማዕድን ማውጫው ውስጥ ላlllu ሌሎች ልጆች ተናግረው ይሆን?

**35.** አቶ ካሳሁን: ምንድን ነው የምትይው ለምለም፤ ሁሉንም ጠይቄ ነበር። ገንዘብ ሁላ ሳይቀር ሰጥቼያቸዋለሁ። ማንም ግን የእነዚህን ምጥማጦች ዱካ የሚያሳየኝ አላገኘሁምል።

**36.** ወ/ሮ ለምለም: ጥሩ። እንደው ሳሰላስል በአይምሮዬ ይህ ብልጭ ብሎብኝ ነው። **(short pause)** ካሳሁን?

**37.** አቶ ካሳሁን: ምንድን ነው ደግሞ?

**38.** ወ/ሮ ለምለም: ዛሬ ልንገናኝ እንችላለን?

**39.** አቶ ካሳሁን: ጎልፍ ክለብ ዛሬ ማታ ከአንድ ጓደኛዬ ጋ ልንገናኝ ቀጠሮ ይዣለሁ። ደግሞ ከመጠየቅሽ በፊት ነው። ለስራ ጉዳይ ነው።

**40.** ወ/ሮ ለምለም: ከዛ በኋላ መምጣት እችላለሁ?

**41.** አቶ ካሳሁን: ለከት ይኑርሽ ለምለም። ሲጀመር እኔ የስራ ሰው ነኝ።

**42. MUSIC INTERLUDE**

## SCENE 2: በለጠ WITH THE SECURITY GUARD AT THE SCHOOL GATE

**43. DORMITORY ATMO**

**44. SFX: KNOCK ON WOODEN BOOTH**

**45. በለጠ:** እንደምን አሉ የጥበቃ ሰራተኛ

**46. GUARD:** ማነህ? እረፍት ላይ ነኝ።

**KW BEGIN**

**47. በለጠ:** ነው እንዴ ይቅርታ

**48. GUARD:** ምን ፈልገህ ነው? ወቸ ጉድ ጊዜዬን እያቃጠልክ እንደሆነ ይገባሃል?

**49. SFX: FOOTSTEPS COMING OUT OF BOOTH**

**50. በለጠ:** **(cheerful)** በለጠ ጀምበሬ እባላለሁ። እዛ ጠርዙ ላይ 5ኛ ዶርም ነው ክፍሌ። እንዴት ነዎት?

**51. GUARD:** **(not interested)** አንተ ጎረምሳ፤ ምን ዳር ዳር ትላለህ፤ ምን ፈልገህ ነው?

**52. በለጠ:** **(still cheerful, but cautious)** እያይ…እርስዎን ለመረበሽ ወይንም ለማስቀየም ብዬ አይደለም። የትምህርት ቤታችንን ግቢ በአግባቡ እየጠበቁ መሆንዎን ስለማውቅ እንደው ትንሽ ላጫውትዎ ብዬ ነው።

**53. GUARD:** አንተ ልጅ፤ ጭንቅላት የለህም እንዴ? ለመሆኑ አንጎል ነው  ወይንስ ገንፎ እዚህ ጠባብ ጭንቅላት ውስጥ የተሸከምከው? ለወሬ አይደለም እዚህ የምመጣው፤ ይህ ቢሮዬ ነው አንተ ደደብ።

**KW END**

**54.** በለጠ: (surprised) ጥሩ… የመጣሁበትን ጉዳይ ልንገርዎ

**55.** **GUARD:** አዎን። ይሻልሃል። ደሞ አፍጥነው።

**56.** በለጠ: **(thinking aloud)** ለመናገር ትንሽ ይከብዳል… **(to Guard)** እእ … ይሄውልዎ። ለእርስዎ ትንሽ ስጦታ ቢጤ ናት። **(jokes)** ምናልባት ዕረፍት ሲያደርጉ ዘና ሊሉባት ይችላሉ። **(holds out package of cigarettes)**

**57.** **GUARD:** ወይጉድ!

**58.** **SFX: PACKAGE OF CIGARETTES HANDED OVER**

**59.** **GUARD**: **(hesitates)** ወቸ ጉድ… ለምን?… ደግሞ ሲጋራ አጫሽ መሆኔን በምን አወክህ?

**60.** በለጠ: ምንም አይደለም። ጓደኛዬ እና እኔ ብቻ ነን ስለዚህ የምናውቀው። ለትምህርት ቤቱ ኃላፊም አንናገርም። በተጨማሪም… ይህቺን ነገር ለእርስዎ አምጥቻለሁ።

**61.** **SFX: BANK NOTES BEING HANDED OVER**

**62.** **GUARD:** **(surprised)** መልካም አመሰግናለሁ። ግን ለምን ሲባል ነው እነዚህን ስጦታዎች የምትሰጠኝ?

**63.** በለጠ: ይህን ያህል ቁም ነገር ያለው አይደለም። ምህረት የምትባል ልጅ ዛሬ ከሰዓት ልትጠይቀኝ ትመጣለች። እባክዎን ስትመጣ እኔ ክፍል አምስተኛው ዶርም ድረስ ደብቀው ያምጧት። በዚህ ከተባበሩኝ ሌላም ትንሽ ነገር ይጨመርልዎታል።

**64.** **GUARD**: **(pleasantly)** እሺ. አመሰግናለሁ። የተቻለኝን ሁሉ አደርጋለሁ።

**65.** በለጠ: በጣም አሪፍ። ይኼው ነው። አሁን ጓደኞች ነን ብዬ እገምታለሁ።

**66.** **GUARD**: በትክክል።

**67.** **MUSIC INTERLUDE**

**SCENE 3: ምህረት TALKS TO ትዕግስት IN THE SCHOOL LIBRARY ABOUT ዳንኤል 'S INVITATION**

**68.** **SFX: SCHOOL LIBRARY ATMO**

**69.** ትዕግስት: **(whispering)** በጣም አዝናለሁ።እናትሽ እንዲህ ጥለውሽ ሲሄዱ ነገሮች ሁሉ በአሁኑ ሰዓት ከባድ እንደሚሆኑብሽ ይገባኛል። ግን እንዴት ነሽ?

**70.** **SFX: PAGES OF A BOOK BEING TURNED**

**71.** ምህረት: **(whispering)** እረ አትጬሂ ትዕግስት። ቤተ መፅሀፍት ውስጥ እንዳለን እረሳሽው እንዴ። ግን ልክ ነሽ። ይከብዳል። ብቻ በቅርቡ ተመልሳ በመጣች። ብቻዬን ከአባቴ ጋ አልቋቋመውም። እሱ ለራሱ… ግራ… የሚያጋባ ነው።

**72.** ትዕግስት: **(laughs cheekily but in hushed tone)** ይገባኛል።

**73.** **LIBRARIAN**: **(far away) (clears throat)** ልጆች።አባካችሁ ፀጥ በሉ። ይህ ቤተ መፅሀፍት እንጂ ገበያ አይደለም።

**SILENCE**

**74.** **SFX: PAGES OF BOOK TURNED AGAIN**

**75.** ምህረት: ባክሽ ትዕግስት ከዚህ የበለጠ ሌላ ችግር ገጥሞኛል።..

**76.** ትዕግስት: (sarcastic) ሚስኪን ምህረት! ደግሞ አሁን ምንድን ነው?

**77.** ምህረት: (shyly) ዳንኤል። ዛሬ ከሰዓት በኋላ መኝታ ክፍሉ እንድመጣ ጠይቆኛል። እንደውም አሁን እየጠበቀኝ መሰለኝ።

**78.** ትዕግስት: (little jealous) ወይኔ...ጉድ..ፈላ... ዛሬ...

**79.** ምህረት: ቀልድሽን አቁሚ ትዕግስት። ከምሬ ነው። በጣም ነው የፈራሁት። ቅር ላሰኘው አልፈልግም። በሌላ በኩል ደግሞ ነገሩ ልክ አይደለም። ምን ባደርግ ይሻላል ትያለሽ?

**KW BEGIN**

**80.** ትዕግስት: (serious tone) በይ ምህረት። በመጀመሪያ ነገር አታካብጂ። ሁለተኛ ደግሞ እንድትመጪ ብቻ ነው የጠየቀሽ አይደል፤ መቼም ከዚህ ያለፈ ነገር አልጠየቀሽም ፤ ትክክል?

**81.** ምህረት: ልክ ነሽ።

**82.** ትዕግስት: አንቺ ደግሞ ትፈልጊዋለሽ አይደል? ማለቴ ከሌሎች ወንዶች አስበልጠሽ ትወጂዋለሽ? ።

**83.** ምህረት: አዎ። ግን...KW END

**84.** ትዕግስት: እኔ አንቺን ብሆን ኖሮ እዚህ ቤተ መፅሀፍት ተቀምጬ እያነበብኩ ራሴን አልበጠብጥም ነበር።

**85.** ምህረት: ምን ማለትሽ ነው፤ ፈተና እኮ ደርሷል...

**86.** ትዕግስት: አዎ ቢሆንም –ለእዚህ ጉዳይ እራሴን አዘጋጅ ነበር።

87. ምህረት: (confused) እንዴት? እንደዚህ ስትይ ምን ለማለት ነው?

88. ትዕግስት: ውይ! የሆንሽ ጅል ነገር ነሽ። አንዳንዴ እንደውም እንዴት ጓደኛዬ ልትሆኚ እንደቻልሽ ይገርመኛል። ማለቴ አንቺ እና እርሱ ብቻችሁን ስትሆኑ የመጀመሪያችሁ መሆኑ ነው። ለመሆኑ እንዴት አድርገሽ ነው እርሱ ክፍል የምትገቢው?

89. ምህረት: (baffled) እ... እኔንጃ...አላውቅም። እሱን ለኔ ተይው ብሎኛል። ግን ትዕግስት አንድ ሰው ቢያየኝስ? ከትምህርት ቤት ሁላ ልባረር እችላለሁ። ያ ደግሞ እንዲሆን አልፈልግም።

90. ትዕግስት: እንዴት አድርጎ ደብቆ እንደሚያስገባሽ ለማወቅ ጓጉቻለሁ። ምናልባት ከሱ አንዳንድ ሽወዳዎችን መማር እችላለሁ። (chuckles)

91. ምህረት: በይ እንሂድ (hesitates) ትዕግስት? ዳንኤል ክፍል አብረሽኝ ትሄጃለሽ?

92. ትዕግስት: ሞኝ አትሁኚ ምህረት። የተጋበዝሽው አንቺ እኔ ምን ቤት ነኝ። ይልቅስ ተዝናኚ። በቅርቡ ተገናኝተን ስለሆነው ሁሉ ታጫውቺኛለሽ።

93. SFX: CHAIR BEING PUSHED BACK

94. SFX: HURRIED FOOTSTEPS APPROACHING

95. ትዕግስት: (not amused) ኡህ ምህረት - ጉዳችን ፈላ...

96. LIBRARIAN: (angry voice) ፀጥ ትላላችሁ ፀጥ በሉ። ካለበዚያ ውጡና ሂዱ።

97. ትዕግስት & ምህረት: ይቅርታ።

98. ትዕግስት: (whispering to ምህረት) በይ ሂጂ ምህረት! የሆነውን እስክሰማ ጓጉቻለሁ።

**99.** ምህረት: በይ እሺ… ቻው።

**100. SFX: CHAIR BEING PUSHED BACK**

**101. MUSIC INTERLUDE**

## SCENE 4: THE GUARD SNEAKS ምህረት INTO ዳንኤል 'S ROOM

**102. DORMITORY ATMO**

**103. SFX: QUIET FOOTSTEPS ARRIVING**

**104.** ምህረት: **(taking a deep breath, speaking to herself)** ማንም የሌለ ይመስላል። አንድ ሰው ሳያየኝ ፈጠን ልበል።

**105. SFX: FOOTSTEPS CONTINUE**

**106. GUARD**: **(annoyed)** ማነው?

**107. SFX: STEPS STOP**

**108. SFX: GUARD GETTING UP FROM HIS CHAIR**

**109.** ምህረት: **(timid voice)** ኦ ይቅርታ አላየዎትም ነበር።

**110. GUARD**: **(realizes)** ኦ ልጅቷ አንቺ መሆን አለብሽ።

**111.** ምህረት: ልጅቷ? የትኛዋ ልጅ? አንድ ነገር ልጠይቅዎ ነበር። --

**112. GUARD**: **(cuts her short)** አትጠይቂኝ። ምንም መልስም የለኝ። ፈጠን በይ። ተከተይኝ፤ ወደ ዶርም አምስት እወስድሻለሁ።

**113.** ምህረት: ዳንኤል የሚኖረው እዚያ ነው? ዶርም አምስት?

**114. GUARD**: ጥያቄ አልፈልግም። አርፈሽ ተከተይኝ ብዬሻለሁ።

**115. SFX: HURRIED FOOTSTEPS WALKING ON STAIRS**

**116. GUARD**: ልጅት ፍጠኚ ነው የምልሽ። ወደ ውስጥ ስንገባ ማንም እንዲያየን አልፈልግም።

**117. SFX: GATE BEING UNLOCKED AND LOCKED AGAIN**

**118. GUARD**: በይ ግቢ። ዶርም አምስት ጠርዝ ላይ ያለው ክፍል ነው።

**119.** ምህረት: **(scared voice)** ቆዩኝ፤ ስመለስስ እንዴት ነው የምወጣው?

**120. SFX:** ምህረት **STEPS IN**

**121. GUARD**: ያ የራሳሽ ድርሻ ይሆናል። አሁን ወደ ቢሮዬ መመለስ አለብኝ።

**122. SFX: GUARD LOCKS GATE AGAIN**

**123. MUSIC THEME INTERLUDE**

**124. <u>OUTRO – NARRATOR:</u>**

በእዚሁ 15ኛው ክፍል መደምደሚያ ላይ ደርሰናል። ምህረት ሹልክ ብላ የወንዶች ማደሪያ ክፍል ገብታ ከዳንኤል በጥቂት ሜትሮች ርቀት ላይ ቆማለች። ቀጥሎ ምን ይከሰት ይሆን? «መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ» የሚለውን ቀጣይ የበማድመጥ መማር ድራማ ይከታተሉ። አስታውሱ ይህንን እና ሌሎች ክፍሎችን ደግመው መስማት ከፈለጉ dw.de/lbe የተሰኘዉን ድረ- ገፃችንን ይጎብኙ፤ አልያም በፌስቡክ አድራሻችን ላይ ይከታተሉ። እስከሚቀጥለዉ ዝግጅት ድረስ ጤና ይስጥልን።